# የወር አበባ ክልከላዎች እና ማኅበራዊ ተጽእኖዎቻቸው፡- በካፋ ዞን ማኅበረሰብ ተተኳሪነት

የኔዓለም አረዶ[1]፣ ደስታ አማረ[2]፣ ደስታ ደሳለኝ[3] እና ፍሬሕይወት ባዩ[4]


**አጠቃሎ**

ይህ ጥናት ከወር አበባ ጋር የተያያዙ ልማዳዊ ድርጊቶችን ማጥናት ላይ አተኩሯል። ዋና አላማው ከወር አበባ ጋር በተያያዘ ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ማህበራዊ ተጽእኖ ማሳየት ነው። ጥናቱ በካፋ ዞን በሚገኙ የካፋቾ፣ የናኦ እና የጻራ ብሔረሰቦች ላይ ተወስኗል። መረጃዎች ምልከታና ቃለ መጠይቅን በመጠቀም ተሰብስበዋል። በመረጃ ሰጪነት ወንዶችም ሴቶችም እንዲሁም ለመረጃ ማስተንተኛነት የማህበራዊ ውክልና ንድፈ ሀሳብ ተመርጠዋል። መረጃዎቹ እንደሚያመለክቱት አንዲት ሴት የወር አበባ ስታይ ከቤት ትወጣለች፤ ውሎዋና አዳሯ ከዋናው ቤት ውጪ በተሰራች አነስተኛ መጠለያ ውስጥ ይሆናል፤ እርሷ ያዘጋጀችውን ምግብ ሌላ ሰው አይመገብም፤ በተለይ እርሷ ያዘጋጀችዉን ምግብ ባለቤትዋ ከተመገበ ከባድ ችግር ይከሰታል ተብሎ ይታመናል። የወር አበባ እየታያት እቤት ውስጥ ከገባች ውቃቢ ይጣላታል፤ ልትታወር ትችላለች፤ ልትሞትም ትችላለች የሚል እምነት አለ። በመሆኑም በመኖሪያ ቤትዋ ውስጥ እያለች ድንገት የወር አበባ ቢታያት፣ ከቤትዋ ወጥታ ስትመለስ የመንጻት ሥርዓት እንዲፈጸምላትና ሁኔታዎችን እንድታመቻች ባህሉ ያስገድዳታል። በጥናቱ ውጤት መሰረት በተጠኑት ብሔረሰቦች ሴትነት በተለይ ከወር አበባ ጋር ተያይዞ የሀጥያት እና ንጹህ ያለመሆን ትዕምርት ተደርጎ ይወሰዳል። አንዲት ሴት የወር አበባ በምታይባቸው ቀናት ከቤተሰብ እንድትነጠል የሚያስገድደው ልማድ በመኖሩም ሴቷ በማኅበራዊም ሆነ በስነልቦና ረገድ የሚደርስባት ተጽእኖ ከፍተኛ ነው። የወር አበባ ለአቅመ ሄዋን የመድረስ መገለጫ ነው፤ ዘር ይቀጥል ዘንድ ተፈጥሮአዊ ጸጋ የሆነው የወር አበባ ሚናም የላቀ ነው፤ በመሆኑም ይህን ማኅበረሰቡ ተረድቶ ሴቶችም አስፈላጊውን ጥንቃቄ እያደረጉ በቤታቸው እንዲቆዩ አልያም መገለል እንዳይደርስባቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በሚመለከታቸው አካላት ቢሰራ መልካም ነው።


ቁልፍ ቃላት፡- [የወር አበባ፤ ሀገረሰባዊ እምነት፣ ካፋ፣ተጽእኖ፣ ክልከላ]


[1] ፒኤችዲ፤ በቁሳዊ ባህል ረዳት ፕሮፌሰር፣ አማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት ጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ Email yenealem2006@yahoo.ca

[2] ፒኤችዲ፤ በሀገረሰባዊ ልማድ ረዳት ፕሮፌሰር፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ Email desta_amare@yahoo.com

[3] ፒኤችዲ፤ በስነቃል ረዳት ፕሮፌሰር፣ የማህበራዊ ሳይንስና ቋንቋ ትምህርት ክፍል፣ ስነትምህርትና ባህሪይ ጥናት ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ Email desalegndesta@gmail.com

[4] ፒኤችዲ፤ በሀገረሰባዊ ልማድ ረዳት ፕሮፌሰር፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ Email firebayu@gmail.com

## 1. መግቢያ

በብዙ የአፍሪካ ማኅበረሰብ ዘንድ የወንዶች የበላይነትና በሴቶች ላይ የሚደርሰው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ በዘርፉ ምርምር ያካሄዱ ተመራማሪዎች (Dejene 2009፤ Obi 2005) ይገልፃሉ።በባህልና እምነት ስም ሴቶች ከሚጨቆኑባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የወር አበባ ነው። ይህ ጥናት በካፋ ዞን ማኅበረሰብ በወር አበባ ወቅት ከማኅበረሰቡ እምነት ጋር ተያይዞ ለሴቶች የሚፈቀዱ እና የሚከለከሉ ነገሮች ምንድናቸው? ምን ተጽዕኖስ አላቸው? የሚሉት ጉዳዮች ላይ አተኩሮ የተካሄደ ነው።

የወር አበባ ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ልጃገረዶችና በአማካይ ዕድሜያቸው 45 ያልበለጡ ሴቶች ላይ በየወሩ የሚታይ (የሚከሰት) የተፈጥሮ ዑደት እንደሆነ Brantelid እና ሌሎች (2014) እና Danielsson (2017) ያስረዳሉ። የወር አበባ ተፈጥሮአዊ ክስተት ይሁን እንጂ ጉዳዩን የሚመለከቱ እሳቤዎች መሰረታቸው ባህል ነው። ይህንኑ Walton, (2013:16) ሲገልጹ "While menstruation is universal, how we deal with it is very culturally specific" ብለዋል። የወር አበባ ምንጩ ተፈጥሮ ሆኖ ሳለ ጉዳዩ ከባህል ጋር በጥብቅ የተሳሰረ እንዲሁም አተገባበሩ ከባህል ባህል የተለያየ እንደሆነ የቀረበው ሀሳብ ያመለክታል። ከዚህ የተፈጥሮ ኡደት ጋር የተያያዘ አመለካከት በሴቶች ላይ የሚያደርሰው ተጽእኖ ቀላል የሚባል አይደለም። ተጽእኖውም ጎልቶ የሚታየው በተለይ ዘመናዊ (መደበኛ) ትምህርት ባልተስፋፋባቸው እና ጤና ጣቢያዎች በበቂ ሁኔታ ባልተገኘባቸው የገጠር አካባቢዎች[5] ነው። በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ከወር አበባ ጋር ተያይዞ ሰርጾ ያለው ልማድ በሴቶች ላይ ተጽእኖ ሲያደርስ ይስተዋላል። ለዚህ ደግሞ በካፋ ዞን በገጠር የሚኖሩ ሴቶች ላይ የሚደርሰው ጫናና መገለል ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡

የካፋ ዞን በደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ ዞኖች መካከል አንዱ ሲሆን በ12 ወረዳዎችና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች የተዋቀረ ነው። ዞኑ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅና በሰሜን ምዕራብ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ከጅማ ዞን፣ በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ከኮንታ ዞን፣ በደቡብ ከደቡብ ኦሞ ዞን፣ በደቡብ ምዕራብ ከቤንች ማጂ ዞንና በምዕራብ ከሸካ ዞን ጋር ይዋሰናል (የዞኑ ባህልና ቱሪዝም የጽሑፍ መረጃ፣ ታህሳስ 8፣ 2014 ዓ.ም) ።

የካፋ ዞን በቂ ጥናት ያልተካሄደባቸው ባህሎችና የፎክሎር ዘርፎች[6] አሉት። በዞኑ በዋናነት የሚገኙት ሶስቱ ብሔረሰቦች (ካፋቾ፣ጻራ እና ናኦ) የራሳቸው የሆኑ ባህላዊ መገለጫዎች አሏቸው። ከነዚህ ውስጥ ዱሞ/ማራማይ (ክፉ ነገር ሲሰማ ባገቡ ሴቶች አማካይነት የሚከወን የመንፃት ስርዓት)፤ የእርቅ ስርዓት፤ ልዩ የዘመን አቆጣጠር፤ ከጤፍ አመራረት ጋር የተያያዙ ባህላዊ ስርዓቶች፣ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ፣ የነገስታት መካነ መቃብርና ከመቃብሮቹ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ አፈ-ታሪኮች፣ ከእንስት ተክልና ከተክሉ ውጤት የሚሰሩ የምግብ አሰራር ጋር የተያያዙ ማህበረሰባዊ እምነቶች፣ እንዲሁም በስፋት ያልተጠኑ ሌሎች የፎክሎር ዘርፎችን መጥቀስ ይቻላል። በተጨማሪም በወሊድ ወቅት የሚከወን ባህላዊ ስርዓትና ከስርዓቱ ጋር የተያያዙ ባህላዊ እምነቶች በተለይ ሴቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ትኩረት የሚሹ ናቸው። ይህ ጥናትም በብሄረሰቦቹ ከሚከወኑ

[5] ከከተማ አካባቢ ራቅ ያሉና ትምህርት ቤቶች፤ ጤና ጣቢያዎች በበቂ ሁኔታ ያልተዳረሰባቸው አካባቢዎች

[6] እንደ Dorson (1972) ፎክሎር አራት ዘርፎች አሉት፡፡ እነርሱም ስነ ቃል፣ ቁሳዊ ባህል ሃገረሰባዊ ልማድ እና ትውን ጥበባት ናቸው፡፡

ከሴቶች ጋር የተያያዙ ልማዶች መካከል ከወር አበባ ጋር የተያያዙ ልማዶችን ማህበራዊ ተጽእኖ መመርመር ላይ ተወስኗል።

ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከወር አበባ ጋር ተያይዞ በሴቶች ላይ የሚደርሰው ጫና እና ክልከላ በዞኑ ገጠራማ አካባቢዎች እየተተገበረ ይገኛል። ባህላቸውን መጠበቃቸው በጎ ጎን ቢኖረውም በማኅበረሰቡ ክፍሎች ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩት ግን ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊጠኑ ይገባል። ለዚህ ማስረጃ እንዲሆን የሚከተለውን ሀሳብ መመልከቱ ተገቢ ነው። “Menstruation is stigmatized in our society. This stigma built up due to traditional beliefs in impurity of menstruating women and our unwillingness to discuss it normally” (Bhartiya 2013:253). ፅሁፉ የሚያትተው ሴቶች በተለይ የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት ያልጸዱ አድርጎ የማየት ባህላዊ ልማድ እና ስለጉዳዩ በግልጽ ያለመነጋገር ችግር የቆየ መሆኑን ነው። ይህም በመሆኑ የወር አበባን የሚመለከት አሉታዊ እሳቤ በሰዎች አእምሮ ተቀርጾ እንዲቀር ባህላዊ እና ልማዳዊ አመለካከቶቹና ድርጊቶቹ ጉልህ ተጽእኖ አላቸው።

በሃገራችን የሚገኙ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ከወር አበባ ጋር በተያየዘ የተለያዩ ግምቶች ሲሰጡ ኖረዋል (Muriricho (ND)። አሁንም በተለይም በገጠሪቱ የሀገራችን ክፍሎች እነዚህ እሳቤዎችና አመለካከቶች ሴቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና በዘነጋ መልኩ ሲንፀባረቁ ይስተዋላል። ይህንኑ መሰረት በማድረግ ይህ ጥናት እንዲካሄድ ምክንያት የሆኑ ዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው።

የወር አበባ የሰው ልጅ በዚህ ምድር ላይ እንዲኖር እና ዘር እንዲቀጥል የማይተካ ሚና ያለው መሆኑ ትኩረት እንዳይሰጠው ምክንያት የሆኑ ባህላዊና ልማዳዊ አሳቤዎች ምን እንደሆኑ ለይተን ለማወቅ ያለን ፍላጎት አንዱ ነው። አሁን ባለንበት ዘመን ስለሴቶች ጉዳይ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እና የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ቢሆንም ይህ ባህላዊ ጉዳይ በማኅበረሰቡ ዘንድ እንዲቆይ ያደረጉ ጉዳዮችን መለየትና ማጥናት ለሴቶቹ ብሎም ለማኅበረሰቡ ጠቃሚ አበርክቶ ይኖረዋል ብለን በማሰብም ጭምር ነው።

ሌላው ይህንን ጥናት ለማካሄድ ምክንያት የሆነን በአካባቢው በተገኘንባቸው የተለያዩ አጋጣሚዎች[7] ሴቶች በቤት ውስጥ እና ከቤት ውጪ በሚከናወኑ ስራዎች ላይ ተሳታፊነታቸው ከፍተኛ በመሆኑ ነው። ነገር ግን የወር አበባ በሚያዩበት ጊዜ ንጹህ እንዳልሆኑ፣ በአደባባይ መታየታቸውም እንደ ነውር መቆጠሩን መታዘባችን የተቃረነ ሀሳብ ስላጫረብን ጉዳዩ በጥልቀት ቢጠና ማኅበረሰቡን ለማወቅና በጉዳዩ ረገድ ያለውን እሳቤ ለመረዳት ይጠቅማል በሚል ነው።

የጥናቱን ችግር መነሻ ምክንያቶች ከግምት በማስገባት ባደረግነው የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ በጉዳዩ ላይ የተካሄዱ የተወሰኑ ሥራዎችን አግኝተናል፤ የMengistu Boshe (2018) እና የBalew Zeleke (2016) ለኤም ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ እና ትኩረታቸውን በተማሪዎች ላይ ያደረጉ ጥናቶች ናቸው። ሌሎቹ በመጣጥፍ ደረጃ የተሰናዱ ጥናቶች ሲሆኑ Upashe እና ሌሎች (2015) በምዕራቡ

[7] የዚህ ጥናት አቅራቢዎች በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ የተቀናጀ የቡድን ጥናት (thematic research) በካፋ ዞን በነበረ የአራት አመት ቆይታ(ከ2009-2012) በጥናቱ አካባቢዎች በተለያዩ ጊዜያት የመገኘት እና በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መረጃዎችን የመሰብሰብ አጋጣሚ ነበራቸው፡፡

የኢትዮጵያ ክፍል የሁለተኛ ደረጃ ሴት ተማሪዎች ከወር አበባ የተያያዘ የግል ንጽኅና አጠባበቅ እውቀትና ትግበራን መፈተሽ ላይ ትኩረቱን ያደረገ ጥናት አካሂደዋል። *በተጨማሪም* Wall, እና ሌሎች (2018) በሰሜን ኢትዮጵያ ትግራይ አካባቢ ከወር አበባ ጋር የተያያዙ እምነቶችን በሚመለከት፣ Muriricho (ND)ም እንዲሁ፣ በአማራ ክልል ቦሰና ወረና ገጠራማ አካባቢ ያለውን የወር አበባ የሚያዩ ልጃገረዶች እና ሴቶች ህይወት የቃኘ ጥናት አቅርበዋል።

የቀደሙት ጥናቶች የMengistu (2018)፣ የBalew (2016)፣ የ Upashe እና ሌሎች (2015) እንዲሁም የWall እና ሌሎች (2018) ጥናቶች ከእኛ ጥናት የሚለዩበት ዋናው ጉዳይ በከተሞች አካባቢና በተማሪዎች ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ የኛ ጥናት በቂ መረጃ ባልተዳረሰባቸው[8] ገጠራማ በሆነው አካባቢ የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው። የMuriricho (ND) ጥናት ትኩረቱ በገጠራማው አካባቢ ባሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ የተካሄደ መሆኑ ከኛ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም በጥናት ዘዴና በተጠኚው ማኅበረሰብ (ይህ ጥናት የተለያዩ ማህበረሰቦችን በተጠኚነት በመምረጡ) ልዩነት አለው። በመሆኑም የተካሄዱት ምርምሮች በቂ ባለመሆናቸው፣ ምንም እንኳን በመስኮች መካከል በይነዲሲፕሊናዊነት ቢኖርም፣ የተቃኙበት የጥናት መስክ ይህ ጥናት ከተቃኘበት የጥናት ዘርፍ (ፎክሎር) የተለዩ በመሆናቸው፣ የተካሄዱትም በቂ መረጃ ያገኛሉ በሚባሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች (ተማሪዎች፣ በተለይ የWall እና ሌሎች (2018) ጥናት የህክምና ባለሙያዎች፣ መምህራን እና የትምህርት ቤት አመራሮች) ላይ ስለሆነ፣ ርዕሰ ጉዳዩንም ሆነ ማኅበረሰቡን ማጥናት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል።

ይህ ጥናት የካፋ ማኅበረሰብ የወር አበባን አስመልክቶ ያላቸው አመለካከት በምን ይገለጻል? በሚል ዐብይ ጥያቄ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ዋና ዓላማው በካፋ ማኅበረሰብ ከወር አበባ ጋር በተያያዘ ክልከላ ምክንያት የሚያደርሰውን ማኅበራዊ ተጽእኖ ማሳየት ነው። ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፤ ሴቶች የወር አበባ በሚያዩባቸው ቀናት በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚደርስባቸውን የተለያዩ የመገለል አጋጣሚዎችን መጠቆም፣ የወር አበባን አስመልክቶ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚስተዋለውን የተለያየ ልማዳዊ አስተሳሰብ መግለጽ፣ ሴቶች የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት በማኅበረሰቡ ውስጥ ባሉ እምነቶች ምክንያት በማህበራዊ ህይወታቸው ላይ የሚደርሰውን ተጽእኖ ለይቶ መጠቆም ናቸው።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህ ጥናት በካፋ ዞን በሚገኙ ሶስት ብሄረሰቦች ማለትም ካፋቾ፤ ናኦ እና ጳራ ላይ የተወሰነ ነው። የጥናቱ ትኩረትም በወር አበባ ምክንያት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ማኅበራዊ ተፅዕኖዎችን መርምሮ መግለጽ ይሆናል። መረጃው የተሰበሰበው በዋናነት የወር አበባ ከሚያዩ ሴቶች ሲሆን ባህሉን ያውቃሉ የተባሉ የእድሜ ባለጸጋዎችም[9] ተሳታፊ ሆነዋል። በቦታ ረገድ ባሁኑ ጊዜ ባህላዊ ልማዱ የሚተገበርባቸው ገጠራማ አካባቢዎች ተመርጠዋል። በወር አበባ

---

[8] ሳይንስና ቴክኖሎጂ በስፋት የማይገኝባቸው የገጠር አካባቢዎች፣ መደበኛ ትምህርት ቤት ያልተስፋፋባቸውና ህዝቡ በቂ መረጃ ስለማያገኙ በባህላዊ አኗኗር ህይወታቸውን የሚገፉባቸው ቀበሌዎች

[9] የእድሜ ባለፀጋ ሴቶቹ የቀደመ ልምዳቸውን መነሻ በማድረግ ያሳለፉትን ልምድ እንዲያካፍሉን፣አረጋዊያን ወንዶቹም አብረው በመኖር ያካበቱት ልምድ በማጋራት መረጃ መስጠት ላይ ተሳትፈዋል፡፡

ወቅት መደረግ ስለሚገባው የንፅህና አጠባበቅና አያያዝ መመርመር የጥናቱ አካል አይደለም። በተጨማሪም ጥናቱ የወር አበባ ሳይንሳዊ አመጣጥን እንዲሁም በጤናው መስክ ስላሉ ጉዳዮች አልተመለከተም።

## 2. ክለሳ ድርሳናት

ይህ ክፍል ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮችን ይዟል። የመጀመሪያው ጽንሰ ሀሳባዊ ዳራ ሲሆን የሕይወት ሽግግር ደረጃዎች፣ የወር አበባን እና የሴትነት ሚናን የተመለከቱ ጽንሰ ሀሳባዊ መነሻዎችን አካቷል። በቀጣዩ ክፍል የተመረጠው ንድፈ ሀሳብ ጽንሰ ሀሳባዊ ማብራሪያ ቀርቧል።

### 2.1 የጽንሰ ሀሳብ ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የወር አበባን እና የሴትነት ሚናን እንዲሁም ክልከላንና የነውር እሳቤን የተመለከቱ ጽንሰ ሀሳባዊ መነሻዎች በመረጃ ምንጮች ማመሳከሪያነት ተብራርተው ቀርበዋል።

Sims እና Stephens (2005፡110) የሕይወት ሽግግር ደረጃዎች ሰዎች በሕይወት ወደዚህ ምድር እስከመጡበት እና እስከሚለዩበት ባሉት ጊዜያት መካከል የሚከሰቱትን የሽግግር ጊዜያት የሚመለከት እንደሆነ ይገልጻሉ። እነዚህ ደረጃዎችም ውልደት፣ ለዐካለ መጠን መድረስ፣ጋብቻ እና ሞት የሚባሉ ዋና ዋና ሽግግሮችን ያካትታሉ። እነዚሁ ምሁራን አክለውም ሊሚናሊቲ /liminality/ (ሽግግር)ን ማዕከል በማድረግ የሕይወት ሽግግር (ደረጃዎች)ን Gennepን ጠቅሰው እንደገለጹት ደረጃዎቹ በዋናነት ሶስት ናቸው (2005፡111)። እነዚህም preliminlity /መለየት (ቅድመ ሽግግር)፣ liminality /ሽግግር/ እና post liminality /ድህረ ሊሚናል (መቀላቀል) የሚባሉት ናቸው። አንድ ሰው በነዚህ የሕይወት ሽግግሮች ውስጥ ሲያልፍ ባህላዊ ክዋኔዎች ሊኖሩም ላይኖሩም ይችላሉ፤ ክዋኔዎቹም እንደየባህሉ የተለያዩ ይሆናሉ። የወር አበባ ከነዚህ የህይወት ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስር የሚካተት ሲሆን ሴቶች (በተለይ በመጀመሪያ በሚያዩበት ጊዜ) ከአንድ የህይወት ደረጃ (ከህጻንነት) እርከን ወደሌላ (ጉርምስና) ደረጃ የሚሸጋገሩበት ተፈጥሮአዊ ሂደት ነው።

የወር አበባ የሚለው ቃል "Menstruation" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል አቻ ፍቺ ሲሆን የቃሉን ጥንተ አመጣጥ በተመለከተ Gómez-Sánchez እና ሌሎች (2012፡373) ላይ እንደሚከተለው ገልጸውታል። "Etymologically, the term comes from the Latin menstrus, whose origin is in mensis, which means month; this is also one of the reasons why it is called period". ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የቃሉ መሰረት ላቲን ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ ወር የሚል ነው፤ ጸሐፊው እንደሚሉት ቃሉ ወር የሚለውን ትርጉም በመያዙ ምክንያት ወቅቱን የሚጠብቅ መደበኛ የሆነ የሚል እሳቤን ያመላክታል። በሌላ በኩል Brantelid እና ሌሎች (2014:1) የወር አበባን ሲበይኑ "Menstruation is a natural phenomenon for women during their reproductive years" (2014:1) ይላሉ። እንደነዚህ ምሁራን ገለጻ የወር አበባ ተፈጥሮአዊ ክስተት ሲሆን ሴቶች መውለድ በሚችሉባቸው አመታት የሚያዩት ነው።

ስለ ወር አበባ ሲነሳ ወደ አእምሮአችን በቅጽበት የሚመጣው የደም ፍሰት ነው። ደምንና የወር አበባን በማስተያየት Dammery የሚከተለውን ብለዋል።

> Universally we learn that blood is part of life, invisible within the body boundaries, and that its visibility signifies injury or disease and perhaps even death. Menarche, therefore, is a paradox. It is uniquely a blood loss associated with health and an indicator of potential life (Dammery, 2016፡1).
>
> ደም የሚለው ቃል ሲወሳ በልምድም ሆነ በሳይንስ እንደሚታወቀው የህይወታችን አካል ሲሆን በግልጽ የማይታይ ነገር ግን በሰውነታችን ውስጥ የሚገኝ ፈሳሽ ሆኖ ችግር ሲደርስብን ለምሳሌ በቁስል ወይም በአንዳች አደጋ ምክንያት በግልጽ ወጥቶ የሚታይ ተፈጥሮአዊ (አለማቀፋዊ) እውነታ ነው። ከወር አበባ ጋር የተያያዘው ደም ግን በተቃራኒው ከህይወትና ህይወት ከመስጠት ጋር የተያያዘ የጤናማነት መገለጫ ነው።

ከቀረበው ሀሳብ የምንረዳው ደም የህይወታችን አንዱ አካል እንደሆነ ነው። የወር አበባ የደም ፍሰት የሚታይበት ቢሆንም ጸሐፊዋ እንደሚሉት የመጀመሪያው የወር አበባ እላይ ከቀረበው የደም እሳቤ የተለይ ትርጉም ይኖረዋል፤ ይኸውም መፍሰሱ ራሱ የጤናማነት ምልክት ሲሆን እሱም ለዘር መቀጠል አንዱ ማሳያ መሆኑ ነው።

የወር አበባ ተፈጥሮአዊ ክስተት ሆኖ ሴቶች ልጅ መውለድ በሚችሉባቸው አመታት በየወሩ የሚያዩት ነው። የወር አበባ ክስተት ተፈጥሮአዊ ቢሆንም አብረውት የሚነሱ ባህላዊ ጉዳዮች እንደየባህሉ የተለያዩ ናቸው። ከወር አበባ ጋር የተያያዙ ልማዳዊ አመለካከቶችና ድርጊቶች በተለይ ባህላዊ እምነትን በሚከተሉ ማህበረሰቦች ዘንድ መገለጫዎቻቸው የተለያዩ ናቸው።ባህላዊ ድርጊቶቹ በተለይ የወር አበባ በሚያዩ ሴቶች ላይ የሚያደርሷቸው ተጽእኖዎችም አሉ። Gómez-Sánchez እና ሌሎች (2012:373) እንደሚሉት የወር አበባ ተፈጥሮአዊ ቢሆንም ሴቶችና የሚኖሩበትን ማኅበረሰብ የሚያጣምር አስፈላጊ ክስተት ነው። ከወር አበባ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችም ሴቶቹ ከወጡበት ማኅበረሰብ ባህላዊ አውድ ጋር ጥብቅ ትስስር አላቸው። በመሆኑም ጉዳዩና ተያያዥ እሳቤዎቹ ማኅበረሰቡ ለጉዳዩ ያለውን መረጃ፣ እምነት፣ ባህልን መሰረት የሚያደርግ በመሆኑ ከአንድ ማኅበረሰብ ወደሌላ ማኅበረሰብ ሲኬድ የተለያየ ይሆናል። በተለይ ከወር አበባ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ግላዊ እንደሆኑ እንጂ በጋራነት ሊነገርባቸው የማይችሉ ተደርገው ይታያሉ፤ ክልከላም አለባቸው (Nahia et al 2019፡358) ።

በተጨማሪም Danielsson (2017:5) Sommer እና ሌሎች (2015)ን ጠቅሰው እንዳቀረቡት የተለያዩ የስነሰብ ጥናቶች በተለይ ባህላዊ መንገድን በሚከተሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ዘንድ የመጀመሪያው የወር አበባ ለሴቶች አስፈላጊ የህይወት ዑደት ሽግግር እንደሆነ ቢታመንም ከወር አበባ ጋር የተያያዘው ደም ግን የተበከለና ከነውር ጋር የተያያዘ መሆኑን የሚያሳዩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በወር አበባ ምክንያት በሴቶች ላይ የሚደርሰው ጫና የቆየና ስር የሰደደ ጉዳይ እንደሆነና ዛሬም ያልተቀረፈ ችግር ሆኖ መቀጠሉም የተለያዩ ድርሳናት ይገልፃሉ። ለምሳሌ በUNICEF አማካይነት በቡርኪና ፋሶ የተካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው የወር አበባ እንደነውር እየተቆጠረ ዛሬም ድረስ በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ይታያል። “Menstruation remains a taboo in many societies and various negative cultural attitudes and beliefs are still associated with it,” (2013: 6). ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የወር አበባ ነውር እንደሆነና ከወር አበባ ጋር ተያይዘው ያሉ አሉታዊ የሆኑ አመለካከቶች እና እምነቶች ጉዳዩ ነውር እንደሆነ እንዲቀጥል መንስኤ እንደሆኑ ልማዶቹም በአብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍሎች ዘንድ የሚተገበሩ መሆናቸውን ነው። ይህ ጉዳይ አሁን ባለንበት በ21ኛው ክፍለ ዘመንም እየተስተዋለ መሆኑን Danielsson (2017፡ 1) ሲገልጹ “Even in the 21st century in the Western world, where menstruation can be managed in a variety of ways, menstruation remains a subject surrounded by taboos and stigma” ብለዋል። በምዕራቡ ዓለም እንኳን ከወር አበባ አበባ ጋር የተያያዙ እሳቤዎች ጉዳዩን አይነኬና ክልክል እንደሆነ እንዲቀጥል አድርገውታል።

ድርሳናት እንደሚያመለክቱት በልማዳዊ እምነቶች ብቻ ሳይሆን በየአለም በሚገኙ ሀይማኖቶች የወር አበባ ነውር እና አይነኬ ጉዳይ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህም በቀጥታ የሚመለከተው የወር አበባ የሚያዩ ሴቶችን ይሆናል። እንደ Bhartiya (2013፡ 523) ገለጻ “All religions of the world have placed restrictions on menstruating women. Be it Judaism, Christianity, Islam, Hinduism or Buddhism”። ከቀረበው ፅሁፍ የምንረዳው የዓለማችን ሀይማኖቶች ክርስትና፣ እስልምና እና ሌሎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በወር አበባ አማካይነት ሴቶች ላይ የሚጥሉት ክልከላ አለ። ጫናዎቹም የወር አበባ በሚመጣባቸው ጊዜ የሚከለክሉ፤ እንዲታቀቡ የሚያስገድዱ እና እንዲገለሉ የሚያደርጉ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ በሀገር ደረጃ በሩሲያ ክርስቲያኖች ዘንድ ሴት ልጅ በወር አበባ ወቅት ቤተ ክርስቲያን አትገባም። በተጨማሪም ሰውን አተኩራ ካየች እንኳን አየር ይበከላል ተብሎ ስለሚታመን ጥንቃቄ እንድታደርግ ልማዱ ያስገድዳታል። በተጨማሪም እንደBhartiya (2013፡524) ገለጻ አንዲት ሴት የወር አበባ በምታይበት ወቅት ለዚህ ተብላ በተሰራችው ጎጆ ውስጥ መቆየት ይኖርባታል፤ ከወንድ ጋር ግንኙነት እንዲኖራት አይፈቀድም፤ የምትመገበው ምግብም የተወሰነላትን ብቻ ነው፤ እንዲሁም ትኩስ ወይም ጥሬ ምግቦችን እንድትነካ አይፈቀድላትም፤ ትከለከላለች።

የቀደመው ገለፃ እንደሚያስረዳው በሩሲያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ የወር አበባ እንደ ነውር ይቆጠራል። ሴቶች በወር አበባ ወቅት ከሰዎች ጋር መነጋገርና አብሮ መቆየት ቀርቶ አተኩረው የመመልከት ተፈጥሮአዊ ነፃነታቸውን ይነፈጋሉ። የሚሄዱበት ይወሰንላቸዋል፤ የሚመገቡት ምግብ በፍላጎታቸው ሳይሆን በሌሎች ፍላጎት የሚወሰን ይሆናል። ይህም የሚያሳየው በወር አበባ ላይ ያለው አመለካከት በሴቶቹ ላይ ከፍተኛ አካላዊ፣ ማኅበራዊና ስነልቦናዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑን ነው።

በሌላ በኩል በክርስትና ሃይማኖት የወር አበባ ሴቶች በስልጣን ረገድም ተሳትፎ እንዳይኖራቸው የሚያሳድረው ተጽእኖ እንዳለ Bhartiya ሲገልጹ፡ “The history of menustrual taboo has been a major reason to keep women from positions of authority in

Christianity (2013፡ 523) ብለዋል። የቀረበው መልዕክት በክርስትና ሃይማኖት ከወር አበባ ጋር የተያያዙ እምነቶች እንደነውር የሚያስቆጥሩት በመሆናቸው ሴቶች በሃላፊነት ደረጃ እንዳይሳተፉ ምክንያት ሆኗል የሚል እሳቤን ይዟል። ይህ ደግሞ በክርስትናው ለሴቶች ስልጣን የማይሰጥበት ምክንያት ሴቶች የወር አበባ በሚያዩበት ቀናት በቤተሰብ መሃልም ሆነ በአደባባይ እንዳይታዩ የሚከለክል የቆየ ከወር አበባ ጋር የተያያዘ ክልከላ በመኖሩ ነው። አሁንም ድረስ በአንዳንድ ሃይማኖቶች ሴቶች በከፍተኛ የሃይማኖታዊ ስርዓቶች አተገባበር ዋና ከዋኝ ሲሆኑ አይስተዋልም፤ የዚህ ክልከላ ታሪካዊ አመጣጡ ከወር አበባ ጋር ሊያያዝ እንደሚችል በድርሳናቱ ከቀረበው ገለጻ በመነሳት መገመት ይቻላል። ስለዚህ የወር አበባን ምክንያት በማድረግ ሴቶች ነፃ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው ሆኖ ቆይቷል። እስከ አሁንም በተለያዩ ሀገራትና አካባቢዎች እንደ ቀጠለ ይገኛል።

ከወር አበባ ጋር የተያያዘው ልማዳዊ እሳቤ በክርስትናው ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥም ይስተዋላል። በእስልምና ሃይማኖት ሴቷ በወር አበባ ወቅት መስጊድ እንድትገባ አይፈቀድም፤ ቁርዓንንም እንዳታነብ ትከለከላለች (Bhartiya 2013) ። ለምሳሌ በእስልምናው ሃይማኖት ቅዱሱ መጽሀፍ- ቁርዓን ምዕራፍ 2 ቁጥር 222 ላይ የተጻፈውን በመጥቀስ በBhartiya (2013፡524) የሚከተለው ሀሳብ ሰፍሮ ይገኛል። “They ask you about menstruation. Say, ‘It is an impurity, so keep away from women during it and do not approach them until they are cleansed; when they are cleansed you may approach them as God has ordained…” የወር አበባ በሚመለከት ለሚቀርብላችሁ ጥያቄ እሱ ያለመንጻት ነው፤ በዚህ ጊዜ ከሴቶች ራቁ እስኪነጹም ድረስ አትቅረቧቸው። ይላል። በቅዱሱ መጽሐፍ የወር አበባ ያለመንጻት ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል። ከቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን ዋቢ በማድረግ ሴቶች ወደ መስጊድ እንዳይገቡ ቁርዓንንም እንዳይነኩ የሚከለከሉ መሆናቸው በዚሁ ጥናት ተጠቅሶ ይገኛል። በሂንዱ ሃይማኖትም እንዲሁ በወር አበባ ጊዜ ሴቶች ወደ ምግብ ማብሰያ ክፍል እንዳይገቡ ይከለከላሉ፤ ወደማምለኪያ ስፍራ እንዳይገቡ፣ በቀን እንዳይተኙ፣ አበባ እንዳይነኩ፣ ወንዶችንም ሆነ ሌሎች ሴቶችን እንዳይነኩ፣ ጮክ ብለው እንዳያወሩ የሚከለከሉ መሆናቸው ተጠቅሷል። ለዚህም ዋናው ምክንያት በዚህ ጊዜ ሴቶች ንጹህ ያልሆኑና ሌሎችንም የሚበክሉ ተደርገው የሚወሰዱ ተደርጎ የሚታመንም በመሆኑ ነው (Bhartiya (2013፡524)። የወር አበባ እንደ ነውር የሚቆጠርባቸውና ሴቶች የሚገለሉባቸው አጋጣሚዎች በብዙ አገሮች በየልማዶቻቸውና እምነቶቻቸው ሲገለጹ ኖረዋል፤ አሁንም ልማዳዊ ድርጊቶቹ እየተከወኑ ይገኛሉ። ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ቀጥሎ የቀረበው ሀሳብ ነው።

“Many communities taboo physical contact with a menstruating woman, believing that it pollutes males in particular; some Orthodox New York Jews will avoid public transport, lest they sit where a menstruating woman has sat” (Allan, and Burridge 2006 ፡ 5).

የቀረበው መረጃ የሚያመለክተው በብዙ ማህበረሰቦች ዘንድ የወር አበባ ከመጣባት ሴት ጋር አካላዊ ንክኪ መኖር እንደ ነውር ይቆጠራል። በተለይም ከወንዶች ጋር ንክኪ ካላት ወንዶቹ ይበከላሉ ተብሎ ይታመናል። ከነዚህ መገለጫዎች ውስጥ በማስረጃነት የቀረበው አንዳንድ በኒውዮርክ

የሚኖሩ ቀናኢ ወንድ አይሁዶች የወር አበባ የታያት ሴት የተቀመጠችበት ወንበር ላይ ልንቀመጥ እንችላለን በሚል ፍራቻ የሕዝብ ትራንስፖርት ከመጠቀም እንደሚቆጠቡና ለዚህም ምክንያታቸው በአጋጣሚ ሴቷ የተቀመጠችበት ቦታ ላይ ወንዱ ቢቀመጥ ይበከላል /"ይረክሳል"/ ተብሎ መታመኑ ነው።

በተጨማሪም ፊጂ በሚባለው ማኅበረሰብ ዘንድ የወር አበባ የመጣባት ሴት አትክልትና ፍራፍሬ ማሳ ውስጥ እንዳትገባ ፍሬውንም እንዳትነካ ትከለከላለች፤ ለዚህም ዋናው ምክንያት ተክሎቹ ሊደርቁ እስከመጨረሻውም ሊጠፉ ይችላሉ ተብሎ መታመኑ ነው። እንዲሁም እንግሊዝ በሚገኙ የተወሰኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች አንዲት ሴት የወር አበባ መጥቶባት እያለ አትክልቶች የሚገኙበት ማሳ ውስጥ ከገባች እንዲሁም ከነካቻቸው አሳማዎች ወይም አይጦች መጥተው ተክሎቹን ያጠፏቸዋል ተብሎ ይታመናል (Mohamed et al 2018:10)::

የወር አበባ የመጣባቸውን ሴቶች ለማግለል ምክንያት የሚሆኑ እምነታዊ አመለካከቶችና ድርጊቶች እንደየአካባቢውና እንደየባህሉ የተለያዩ እንደሆኑ በተከታታይ ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት ይቻላል። ከላይ የተገለጹት ከሃገረሰባዊ እምነት ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች በካፋ ማኅበረሰብ ዘንድም ጎልተው የሚታዩ ናቸው። በተለይ አሁን ባለንበት የስልጣኔ ዘመንም እየተከወኑ ያሉ ናቸው። ምክንያቶቹን በመለየትና በመመርመር የመፍትሄ ሀሳቦችን ማቅረብ የዚህ ጥናት ትኩረት ነው።

### *2.1.1 የሴትነት እሳቤ እና ማኅበራዊ ሚና*

ሴትነት የሚለው ቃል በስነልቦና፣ በማህበራዊና በባህሪይ ረገድ በውልደት ሴት ለሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች መጠሪያ የሚውል ነው። ሴትነት ከሚለው እሳቤ ጋር የተያያዙ ባህሪያትም በጎነት፣ እርጋታ፣ ተግባቢነት፣ አጋዥነት፣ መረዳት መቻል፣ ተገዢነት፣ ስሜታዊነት እና እናትነት እንደሆኑ Mehta እና Henry (2020፡2) ይገልጻሉ። እነሁ ጸሀፊዎች በተጨማሪ (Darity 2008)ን ጠቅሰው እንዳቀረቡት በተለያዩ መዝገበ ቃላት ውስጥ ሴትነት ከሴት ጾታ ጋር የተያያዙ ባህሪያትን ይመለከታል። በሌላ በኩል (Aragon 2004)ን በመጥቀስ እንዳቀረቡት ሴትነት በወንዶች ተቃራኒ የሆኑ የሴቶች የሆኑ ባህሪያትን ስብስብ የሚመለከት እሳቤ ነው። በቀረቡት ብያኔ መሰረት ሴትነት የሚለው እሳቤ በተፈጥሮ ከሴት ጾታ ጋር የተያያዙ ባህሪያት መገለጫዎችን የሚመለከት ነው። ይሁን እንጂ Mehta እና Henry (2020፡2) ይህ የሴትነት እሳቤ በተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን በባህል፣ በጊዜ፣ በመልክዓምድርና በፖለቲካ ሊገነባ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ አጠንክረው ይገልጻሉ።

ማህበራዊ ሚና በሌላ በኩል ማኅበረሰቡ በግለሰቦች ወይም በቡድን ላይ የጣላቸው ስርዓቶች ወይም ደንቦች ሲሆኑ ከኚሁ አካላት የሚጠበቁ ማህበራዊ ደረጃዎችን እና ቦታዎችን ይወስናል (Dong et al ND:2)። በመሆኑም እነዚህ ስርዓቶች እና ደንቦች የሰዎችን ባህሪያት እና ተግባራት እንዲሁም ከሌሎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይወስናሉ።

በዚህ ጥናትም በተጠኚዎቹ ማህበረሰቦች በወር አበባ አማካይነት ሴትነት የተገለጸባቸውን መንገዶች እና የሚደርሱባቸውን ማህበራዊ ተጽእኖዎች መመርመር ያስችል ዘንድ ቀደም ሲል የቀረቡትን ጽንሰሀሳቦች እና የማህበራዊ ውክልና ንድፈሀሳብ በመጣመር ለመረጃ መተንተኛነት አገልግለዋል።

### 2.1.2 የወር አበባ "ነውርነት" እሳቤ

*ነውር የሚለው Taboo* የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚተካ ሲሆን ከፖሊሽ ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛ በውሰት የገባ ነው (Steiner 1956). Webster (1942:2) ቃሉን ክልከላ በሚል ሲፈቱት በቋንቋ ላይ የተመሰረተ፣ ከባህል ባህል የሚለያይ በየትኛውም የስልጣኔ ደረጃ ባሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ እንደሆነ ይገልጻሉ። በአጠቃላይ ነውር በሁሉም ባህል ውስጥ አለ የሚሉት ደግሞ Abdul-Majeed (2016:401) ናቸው።

ከወር አበባ ጋር የተያያዙ ልማዳዊ ጉዳዮች ከነውር እሳቤ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። እነዚህ በተለይ ከወር አበባ ጋር የተያያዙ ነውር የሚባሉ ጉዳዮችን በሚመለከት Walton (2013፡16) ሲገልጹ፣ ነውር የሚለው እሳቤ በግልጽ ሊነጋገሩበት ወይም ሊሰሩት የማይደፈር/እንዲደፈር የማይፈልግ ወይም የማይፈቀድ ጉዳይ ነው። ጸሐፊው እንደሚሉት በየማኅበረሰቡ የሚገኙ ከወር አበባ ጋር የተያያዙ የነውርነት እሳቤዎች በዋናነት ሴቶች የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት በአደባባይ የሚከወኑ ድርጊቶችና ባህሪያትን የሚከለክሉ ናቸው (2013፡17)። የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የሆነው የወርአበባ እና ልማዳዊ ጉዳዮቹ ከነውር እሳቤ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። በመሆኑም በክልከላው ወይም በነውር ምክንያት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ማህበራዊ ተጽእኖዎችን ለመለየት ያስችል ዘንድ ይህ እሳቤ ትኩረት ተሰጥቶታል።

### 2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

በፎክሎር የጥናት መስክ የተለያዩ ንድፈሀሳቦች አገልግሎት ላይ ይውላሉ። እነዚህ ንድፈሀሳቦችም በተለያዩ መስኮች ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው። በዚህ ጥናትም በስነልቦና ዘርፍ መነሻውን ያደረገው የንድፈ ሀሳብ አይነት ማህበራዊ ውክልና (Social Representations) ከመስክ ለተሰበሰቡ መረጃዎች ማስተንተኛነት ተመርጧል።

የዚህ ንድፈ ሀሳብ ዋና ትኩረት በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለ ጉዳይ ወይም ቁስ አካል በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚሰጠውን ቦታና ውክልና የሚመለከት ነው። Wagner እና ሌሎች (1999፡96) እንደገለጹት "… a social representation is the ensemble of thoughts and feelings being expressed in verbal and overt behaviour of actors which constitutes an object for a social group." ይኸውም ማህበራዊ ውክልና ጉዳዩ ባለበት ቡድን ወይም ማኅበረሰብ ስለጉዳዩ በቃልም ሆነ በተግባር የሚገለጹና ለማኅበረሰቡ ትርጉም የሚሰጡትን እሳቤዎች የሚመለከት ነው። በመሆኑም ጸሐፊዎቹ እንደሚሉት ማህበራዊ ውክልናን ጉዳያቸው የሚያደርጉ ተመራማሪዎች ከማህበራዊ ክስተቱ ጋር የተያያዙ ንግግሮች፣ ልማዳዊ ድርጊቶችና እንቅስቃሴዎችን በአስተውሎት መመልከት አለባቸው።

በአጠቃላይ ማህበራዊ ውክልና ማኅበረሰቡ ለጋራ ተግባቦት አላማ ሲባል ጉዳዩን ወይም ቁሱን የሚገልጽበት አፍአዊ ወይም አፍአዊ ያልሆነ ተግባቦት ወይም ድርጊት ሊሆን እንደሚችል Moscovici (1963፡251) ይገልጻሉ። በመሆኑም በማኅበረሰቡ ዘንድ ጎልቶ የወጣው ጉዳይ የዚያ

ማኅበረሰብ እውነታ ወይም መገለጫ ይሆናል ማለት ነው ። ስለሆነም Botello-Hermosa እና Casado-Mejia (2015፡16) እንደገለጹት በማህበራዊ ውክልና ንድፈ ሀሳብ አተያይ ጉዳዩን በሚመለከት የሚሰጥ ውክልና ረቂቁ ነገር ጎልቶ እንዲታይ፣ አካላዊ እንዲሆን ከማኅበረሰቡ እምነትና አመለካከት ጋር እንዲጣመር ምክንያት ስለሚሆንም ይህ የጋራ ጉዳዩ በሆነው ማኅበረሰብም ተመሳሳይ አመለካከት እና አተያይ እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል። ከቀረቡት ሀሳቦች በመነሳት ይህን ንድፈሀሳብ በወር አበባ ጥናት ላይ መጠቀም ሴቶች ከወር አበባ ዑደት ጋር በተያያዘ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ውክልና ለመረዳት ያስችላል። በተለይ ይህ ንድፈ ሀሳብ ለወር አበባ ጥናት ያለውን አስተዋጽኦ Duveen እና Lloyd (1990፡3) ሲገልጹ “ In short, social representations allows us to know what menstruation means to people, based on both their knowledge and the social discourse concerning the issue”. ማህበራዊ ውክልና ንድፈ ሀሳብ ለሚጠናው ማኅበረሰብ የወር አበባ ምን ማለት እንደሆነና ስለጉዳዩ ያላቸውን እውቀትና ትርጓሜ ለመረዳት ያስችላል ይላሉ። በዚህ ጥናትም ይህን ታሳቢ በማድረግ በካፋ ማኅበረሰብ ሴቶች ከወር አበባ ጋር በተያያዘ የሚሰጣቸውን ቦታ (ድርሻ) ለማጥናት የማህበራዊ ውክልና ንድፈ ሀሳብ ተግባራዊ ተደርጓል።

## 3. የጥናቱ ስነዘዴ

ይህ ጥናት የተካሄደው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በካፋ ዞን በሚገኙ ሶስት ብሔረሰቦች ላይ ነው። በርካታ የጥናት ዘዴዎች ቢኖሩም በፎክሎር ዘርፍ በምርምር የታወቁት ምሁራን እንደ Finnegan (2012) እና Okopehu (1992) ለፎክሎር ጥናት አመቺው የምርምር አይነት አይነታዊ እንደሆነ ይገልጻሉ። በዚህ መሰረት የዚህ ጥናት አይነቱ አይነታዊ ምርምር ነው። አይነታዊ ምርምር የሰዎችን ሀሳብ፣ ስሜት እና ስለአንድ ጉዳይ ያለ እውቀት በቃል፣ በገለጻና በማብራራት መረጃዎች የሚገኙበት፣ የሚደራጁበትና የሚተነተኑበት በመሆኑ ይህም ጥናት ይህንኑ ሂደት የሚከተል በመሆኑ ነው። መረጃዎችን እና የመረጃዎች ምንጮችን በመጠቀም፣ በማፈላለግና በማመቻቸት ረገድ በዓላማ ተኮር የናሙና ስልት የተመረጡት የባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች እና የዞኑ የኮምዩኒኬሽን ሰራተኞችና ጋዜጠኞች አስተዋጽኦ አድርገዋል። እነዚህ ወገኖች ጉዳዩ በቀጥታ ስለሚመለከታቸውና ከማኅበረሰቡ ጋርም ቀጥተኛ ግንኙነት ስላላቸው መረጃ ሰጪዎችን በማግኘት የመስክ ስራው በተፈለገው መንገድ እንዲከናወን ረድተውናል። በተጨማሪም የክልሉ ተወላጆች በመሆናቸው በቃለመጠይቅ ወቅት አማርኛ ተናጋሪ ላልሆኑ መረጃ አቀባዮች የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎችን በመተርጎም እና መረጃዎቻቸውንም ወደአማርኛ በመተርጎም ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። በአጠቃላይ በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ከካፋች፤ ጻራና ናኦ የተገኙ የየብሔረሰቡ ተወላጆች መረጃ ከመስጠትም በተጨማሪ በተርጓሚነት ተባብረውናል። መረጃ በመስጠት የተባበሩን መረጃ አቀባዮችም ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥን በመከተል ተመርጠዋል።

ለዚህ ጥናት ግብዐት የሆኑት መረጃዎች በምልከታና በቃለ መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበዋል። ለምሳሌ ምልከታን በሚመለከት Kothari (2004፡96) እንደገለጹት፤ የምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከባህሪያዊ ሳይንስ ጥናቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። ምልከታ ሳይንሳዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚሆነው ተመራማሪው ስርዓትን፣ መዋቅራዊ እቅድን ይዞ ሲነሳና እርሱንም ተግባራዊ ለማድረግ ሲጥር ነው። ምልከታ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች

በተለየ ተመራማሪው ተጠኚውን ጥያቄ መጠየቅ ሳያስፈልገው በቀጥታ በመመልከት መረጃ የሚሰበስብበት በመሆኑ ነው። በመሆኑም ምልከታ ማንኛውም በአካባቢያችን የሚገኙትንና የማየትና የመታዘብ ሂደትን ብቻ የሚመለከት አይደለም። ይልቁንም ምልከታ ሳይንሳዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለመሆኑ መገለጫው ተመራማሪው ሳይንሳዊ መንገድን ተከትሎ አስቦበትና አቅዶ ሂደቱን ተከትሎ ለማጥናት የፈለገውን ወገን በአካል በማግኘት በሚገባ ከተከታተለ፣ ከቀረፀና የተመለከተውን በሚገባ ከተገነዘበ እንደሆነ Kothari (2004፡96) ያስረዳሉ። በዚሁ መሰረት የዚህ ጥናት አቅራቢዎች የካፋ ማኅበረሰብ ሴቶች በወር አበባ ጊዜ የሚያርፉበትን መቆያ(ማረፊያ) በአካል በመገኘት መመልከትና ከክልከላው ጋር ተያይዞ ያሉ ማኅበራዊ ተጽእኖዎችን ለመታዘብ ችለናል።

ቃለ መጠይቅ በተመሳሳይ ሳይንሳዊ መንገድን በተከተለና የዘርፉ ምሁራን በሚመክሩት መሰረት ለጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል። እንደ Kothari (2004፡97) ገለጻ ይህ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ  ጠያቂው መረጃ አቀባዩን በአካል አግኝቶ ወይም በስልክ በቃል በመጠየቅ የፈለገውን መልስ ለማግኘት የሚያስችለው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው ። በመሆኑም ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለዚህ ጥናት የተጠቀምን ሲሆን በመረጃ አቀባይነት የወር አበባ በሚያዩበት እድሜ ላይ ያሉ ሴቶች፣ ባህሉን የሚያውቁ ወንዶች፣ ጎልማሳዎችና ሽማግሌዎች እንዲሁም የባህልና ቱሪዝም ሰራተኞችን በማሳተፍ መረጃዎችን ሰብስበናል። የተሰበሰበው መረጃም እምነቱን እና ተግባራዊ ልምዱን መሰረት በማድረግና ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ንድፈ ሀሳብ ማሳያነት በገላጭ የትንተና ዘዴ ተተንትኖ ቀርቧል።

## 4. የመረጃ ትንተናና ውጤት

በዚህ ክፍል ከመስክ የተገኙት መረጃዎች በጽንሰ ሀሳብ እና ንድፈሀሳብ ማሕቀፎች እንዲሁም የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ተደራጅተውና ተተንትነው ቀርበዋል።

### 4.1 የወር አበባ ስያሜና አጠቃላይ ዳራ

በጻራዎች ዘንድ የወር አበባ የሚለው ቃል "ኪቻ" በሚል መጠሪያ ይታወቃል። ሴቷ የወር አበባ በምታይባቸው ቀናት የምትጠቀምበት አገላለጽ ደግሞ "ኤቀቀረንቤ" ሲሆን የወር አበባ መጥቶ ከቤት ወጣሁ ማለት ነው። በናኦዎች ዘንድ የወር አበባ "ቃንሶክ" ይባላል። የወር አበባ በምታይባቸው ቀናት ለማረፊያነት የሚሰራላት መጠለያም "ቃንሶ ኢይ" ተብሎ ይጠራል። በካፋዎች ዘንድ ደግሞ የወር አበባ "ዱጶ" ሲሆን የወር አበባ መጥቶ ከቤት ወጥቻለሁ ማለትም "የዎቾ" ትላለች፤ ግራ ወጥቻለሁ እንደማለት ነው።

በካፋ ገጠራማ አካባቢዎች የሚኖሩ ሴቶች (ያገቡና ያላገቡ) በወር አበባ ምክንያት ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የተለያዩ ማኅበራዊ ተጽእኖዎች እየደረሱባቸው ህይወታቸውን ይገፋሉ። አንዲት የወር አበባ የመጣባት ሴት በአማካይ ለአምስት ቀን ወደ ቤቷ መግባት አትችልም። ከቤት ውጪ ከለላ ነገር ይሰራላትና እዚያ ትቆያለች። ጊዜያዊ መጠለያው በአብዛኛው የሚሰራው ከቤትዋ ዋናው በር ቀጥታ ወይም ትይዩ ሳይሆን የቤቱ አባወራ በብዛት በማይተላለፍበት አቅጣጫ ላይ ነው። ለዚህም ምክንያቱ መረጃ አቀባዮች እንደሚሉት ወንዱ የቤቱ ምሰሶ በመሆኑ እርሱ በብዛት በማይሄድበት፣ የቤቱ ምሰሶም በቀጥታ በማይታይበት ቦታ ላይ ይሰራል። መጠለያ መሰሉ ከብርድ የማይከላከልና ለመኝታም የማይመች መሆኑን በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል። ምክንያቱም በዚህ ጊዜያዊ ማረፊያ የሚገኘው መኝታ ከእንሰት ቅጠል የሚሰራ ሲሆን ተደላድሎ ለመተኛት ሳይሆን

እላዩ ለመቀመጥ እንዲቻል ተደርጎ የሚሰራ በመሆኑ ነው። ሴቷ የምትቆይበት ጊዜ /ቀናትም/ የወር አበባ ኡደቱን እስኪጨርስ ሲሆን በእነዚህ ቀናት ወደ ቤቷ የመግባት ፈቃድ አይኖራትም፤ እርሷም ብትሆን ለመግባት አታስብም።

ማኅበረሰቡ የወር አበባን እንደነውርና አለመንጻት አድርጎ ስለሚያምን በአጠቃላይ በአመት በአማካይ አንዲት ሴት ለ60 ቀናት ከመኖሪያ ቤትዋ ውጪ ውላ እንድታድር ትገደዳለች። የወር አበባን በሚመለከት ሁለት አይነት ተረኮች ይነገራሉ። አንደኛው የክርስትናውን ሃይማኖት መሰረት በማድረግ የወር አበባ ሴት (ሔዋን) በፈጣሪዋ ያልተፈቀደውን በለስ በመብላትዋ ምክንያት የደረሰባት መርገምት በመሆኑ በነዚህ ቀናት ንጹኅ እንዳልሆነች፣ ሀጥያተኛ የመሆንዋም ምልክት ተደርጎ በመታመኑ ክልከላው ተግባራዊ የሚደረግ እንደሆነ የሚያትት ሲሆን፣ ሌላኛው የእምነታዊ ልማድ መሰረትን በመያዝ ከየት እንደመጣ ባይታወቅም ሴቶች ላይ የሚታይ፣ በተለይ በአካባቢው በብዛት ተከታይ ባለው በቃልቻ እምነት ልማድ ተቀባይነት የሌለው ተፈጥሮአዊ መገለጫ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑን ከቃለመጠይቅ[10] የተገኙ መረጃዎች አመላክተዋል፡

በናኦዎች ዘንድ እንግዳ እንኳን እቤታቸው መጥቶ ሴትዋ የት እንደሄደች ከተጠየቁ ቤተሰቦቿ ፣"ጉቶ መቷት ወደ ውጭ ናት" ይላሉ፤ በባህሉ በቀጥታ አይነገርም። እንዲህ አይነቱ አገላለጽ የሚታወቅ በመሆኑ ጠያቂውም ከዚህ በላይ ለመጠየቅ አይሞክርም። ከባህሉ ውጪ ለመጣ እንግዳ ሰው ግን መረጃ አቀባዮች እንደሚሉት እውነታው ሊነገረው ይችላል። ይህንንም የቅርበታቸው ሁኔታ ይወስናል። እንግዳው የተከበረና እነርሱ ካመኑበት እንጂ ማንኛውም መንገደኛ የዚህ ዓይነት ጥያቄ ቢያቀርብ ጥሩ አይሆንም። ባህላቸውን እንደናቀ ይቆጠራል።

### 4.2 የሴቶች ሚናና ከወር አበባ ጋር የተያያዙ ክልከላዎች

ጥናቱ በተካሄደባቸው ብሔረሰቦች ዘንድ ሴቶች በርካታ ስራዎችን ይሰራሉ፤ ከቤት ውስጥ እስከ ደጅ ባሉት ስራዎች ተሳታፊ ናቸው። ይህ ጉዳይ በወር አበባ ወቅት ከመገለል ጋር ተያይዞ የሚቋረጥ አይሆንም። የወር አበባ የታያት ሴት በወቅቱ ከቤት ውጭ ብትቆይም ስራ አትፈታም። ደጅ ትጠርጋለች፤ ማገዶ ትለቀማለች፤ እቤቱ ከተለቀለቀ በኋላ በተረፈው አርሷ ደጅ ደጁን ትለቀልቃለች። በአጠቃላይ ወደ ቤት የማያስገቡና ውጪ መከወን ያለባቸውን ተግባራት ታከናውናለች። ነገር ግን ይህቺ ሴት ከበሩ ትይዩ በሚገኝ ሥፍራ እንድታልፍ አይፈቀድላትም። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ካለፈች እንኳን ለምሰሶ የሚሰጠው ክብር ይቀንሳል ተብሎ ይታመናል። ምክንያቱም በማኅበረሰቡ ዘንድ የቤት ምሰሶ የቤቱን ባለቤት (ወንዱን) ይወክላል። ይህንንም ማድረግ እርሱን እንዳለማክበር ተደርጎ ይቆጠራል። በነዚህ ብሔረሰቦች ዘንድ ከወር አበባ ጋር በተያያዘ የጋራ ክልከላ ከሆኑት መካከል ሴቷ የወር አበባ በምታይባቸው ቀናት የእርሻ ማሳ ውስጥ እንድትገባ አለመፈቀዱ አንዱ ነው። ማረም፣ መጎልጎል እና ፍሬዎችን መንካት በፍጹም የተከለከለ ነው።

---

[10] ወይኒቱ ወልዴ፣ ናኦ፣ ኦርቶዶክስ፣ ቀበሌ አገያ ፤ አሊጋነሽ ደምሴ ኦርቶዶክስ፣ ቀበሌ አገያ ፣ቃለመጠይቅ ታህሳስ 09፣ 2014፣ ወርቁ ግዛ፣ ካፉ፣ ኦርቶዶክስ፣ ከተማ ቦንጋ፣ መሰረት መኩሪያ ካፋ፣ ኦርቶዶክስ፣ ከተማ ቦንጋ፣ ቃለ መጠይቅ ታህሳስ 15፣2014)፣ ሙላ ሙልጊቲ ጻራ፣ ቃልቻ፣ ቀበሌ ሻሺ (ቃለመጠይቅ ታህሳስ 23፣2014 ዓ.ም)

ይህ እሳቤ ከማህበራዊ ውክልና ንድፈሀሳብ አኳያ ሲታይ የወር አበባ የሚሰጠው ቦታና ሴቶች የወር አበባ በሚያዩባቸው ጊዜያት በማኅበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ውክልና የሚያመለክት ነው። በዚህ መሰረት የወር አበባ በተጠኚዎቹ ዘንድ ያለመንጻት እና የእርኩሰት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል። በወር አበባ ጊዜ ሴቶቹ የሚነኩት የሚበከል እና የሚበላሽ ለከፋ በሽታ እና ለሞት የሚያበቃ እንደሆነ ተደርጎ እንደሚታመን ከመስክ የተገኙት መረጃዎች ያመላክታሉ። ምክንያቱም እነዚህ (ለምሳሌ ጤፍና በቆሎ) በማንኛውም ጊዜ ለቃልቻ መስዋዕት የሚቀርቡ ስለሚሆኑ ታረክሳለች ተብሎ ስለሚታመን ነው። በተጨማሪም ለተለያዩ ክብረበዓላትም ሆነ ለቃልቻ ለሚቀርብ መስዋዕት የሚዘጋጀው በናይ ጌብዙ የተባለው መጠጥ ከጤፍ የሚዘጋጅ በመሆኑ ጤፉን ከነካችው ይረክሳል ተብሎ መታሰቡ ለክልከላው ምክንያት ነው። ከእህል አይነቶች በተለይ በጻራዎች ዘንድ ሴቷ የወር አበባ በምታይበት ጊዜ ሀረግ ያላቸውን እንደ ቦሎቄ ያሉ የጥራጥሬ እህሎችን ታርማለች፤ ትንከባከባለች። ምክንያቱም እነዚህ የጥራጥሬ እህሎች ለሙት መንፈስም[11] ሆነ ለቃልቻ ዝክር የማይቀርቡ እና ለዕለት ተዕለት የምግብ ፍጆታ የሚውሉ በመሆናቸው ነው።

### 4.3 ከወር አበባ ጋር የተያያዙ ማህበራዊ ተጽእኖዎች

መረጃ ሰጪዎች[12] እንደሚሉት በተለይ ሴትዋ የወር አበባ ይመጣል ብላ በምታስብባቸው ቀናት በራስ መተማመን ማጣት፣ ፍርሃትና አሁንም አሁንም ልብሷን በጥርጣሬ ማየት ታበዛለች። ይህ የሚሆነው ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው የወር አበባ በቤት ውስጥ ሆና እንዳታይ ልማዱ ስለሚከለክላት ነው። በመሆኑም በነዚህ ቀናት የመሳቀቅ እና ከፍተኛ የራስ መተማመን ማጣት ስሜት እንዲሰማት ይሆናል። በተጨማሪም የወር አበባ በምታይባቸው ቀናት ቤተሰቧንም ሆነ የአካባቢውን ማኅበረሰብ የመቀላቀል ነጻነት የላትም፤ ይህም ከተለመደው ማህበራዊ ኑሮዋ እንድትገለል ምክንያት ይሆናል። በአጠቃላይ እነዚህ ጊዜያት በቤተሰቦችዋ እና በማህበራዊ ህይወቷ ላይ የሚያደርሰው ተጽእኖ ከፍተኛ ይሆናል።

በማኅበረሰቡ እምነት የወር አበባ የመጣባት ሴት ከቤት ወጥታ ኡደቱን ጨርሳ እስከምትመለስበት ድረስ በአማካይ ለአምስት ቀናት እቤቷ ምግብ አብስላ አትበላም የሚዘጋጀውንም ምግብ አትመገብም፤ እርሷ ያዘጋጀችውንም ማንም አይበላም። ይህንን እስመልክቶ የካፋ ተወላጅ የሆነችው ወ/ሮ ካሰች ተካ[13] ስትገልጽ፣ “ሴቶች የወር አበባ በሚታያቸው ጊዜ ከቤት ርቀው ነው የሚኖሩት። አንዲት ሴት የወር አበባ በምታይበት ጊዜ ወደ ላይ አትወጣም፤ ባለቤቷንም አታይም። ልጆች ካሏት ልጆችዋ ካልሆነም ጎረቤቶችዋ ምግብ አብስለው ይሰጧታል።” በመሆኑም ሴቷ የወር አበባ አይታ

---

[11] ለሙት መንፈስ የሚቀርብ ዝክር በአካባቢው የሚታወቅ እህል በሚደርስ ወቅት ቤተሰብም ሆነ አብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍል አዲሱን ምርት ከመቅመሱ በፊት በተለይ የአባት ሙት መንፈስን ማመስገኛ እና ማቅመሻ ከበራ ይዘጋጃል፡፡ ከከበራው በፊት እኒህ የእህል ዘሮች ማሳ ላይ እያሉ ማረምም ሆነ መንከባከብ፣ በከበራው ወቅት ለዝክሩ የሚቀርበውን ምግብና መጠጥ ማዘጋጀት፣ መመገብም ሆነ በከበራው ላይ መታደም የወር አበባ ላይ ላለች ሴት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

[12] ወርቁ ወ/ማሪያም፣ ካፋ፣ ታከለ በየነ፣ ናኦ፣ አልጋነሽ ደምሴ፣ናኦ ፣ ወይኒቱ ወልዴ፣ ናኦ ፣ሙላ ሙልጊቲ፣ ጻራ ታደሰ ኦሻሊ፣ ጻራ (ቃለ መጠይቅ 2012)

[13] ቃለ መጠይቅ ታህሳስ 08፣2014 ዓ.ም

ከቤትዋ በምትወጣባቸው ቀናት የዕለት ጉርሷን ማግኘት የምትችለው ልጆች ካሏት በልጆችዋ እንዲሁም በጎረቤቶቿ ድጋፍና ትብብር ነው። ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በባህሉ ጎረቤቶቿ ምግብ አብስለው ባለችበት ቦታ ያቀብሏታል። ይህ ደግሞ እነርሱም በተራቸው ስለሚደርሳቸው እርስ በርስ የሚረዳዱበት አንዱ መንገድ ነው።

አንዲት ሴት የወር አበባ በምታይባቸው ቀናት ባለቤቷ እንዲያያት ልማዱ አይገልጽም። ማየት ብቻ አይደለም የካፋ መረጃ አቀባይ የሆኑት አቶ ወርቁ ወ/ማሪያም እንደሚሉት "ወንዱ የት? ነሽ ምን ሆነሻል? ልብስሽ እንዴት ነው? ውኃ እያገኘሽ ነው ወይ? የሚያስፈልግ ምግብና አልባሳት እያገኘሽ ነው ወይ? የሚል ድጋፍ እስካሁን በባህሉ ጉድለት ይታያል።" በመሆኑም ሴቷ ከማህበራዊ ህይወት መገለል የሚጀምረው ከቤተሰቧ መሆኑን መረጃው ያመላክታል። በተጨማሪም በጻራ ሴቶች የወር አበባ በሚያዩባቸው ቀናት ያለውን የሕይወታቸውን ገጽታ እና እምነታቸውንም ጭምር እንዲህ ሲሉ ገልጸውልናል።

> ቀን ቀን ጓሮ ያለ አትክልት ስናርም፣ ስንኮተኩት እንውላለን። ማታ ቤት መሳይ ጓሮ ውስጥ እናድራለን። በኪቻ ላይ እያለን ከመኖሪያ ቤታችን ባንወጣ ባላችን ሊታመም አይኑ ሊጠፋ ሲከፋም ሊሞት ይችላል። ወይም ሙብረቅ ቤታችንን ሊመታው እና ሳትወጣ የቀረችው ሴት ልትሞት ትችላለች። ሳይወጡ ቀርተው ሞተዋል የሚባሉ ሴቶችን ታሪክ ሰምተናል። ስለዚህ በዚህ ምክንያት ዘራችን እንዳያጥር፤ ልጆቻችን ያ ለእድሜያቸው እንዳይቀጩ፤ ለቤተሰቡ ስንል ባይመቸንም ቢበርድም ደጅ ማደር ቢያሰፈራም አምስት ስድስት ቀን እንቆያለን። ኪቻ መምጣቱን ደብቀን ማንም አያውቅም ብለን በቤታችን ብንቆይ ወይም ኤቀትሳ ባለበት ብንሄድ ቆሌው ያውቃል።[14]

የቀረበው መረጃ ሴቶች በነዚህ ቀናት የእለት ተዕለት ተግባራቸውን ማከናወን የሚጠበቅባቸው መሆኑን ነገር ግን ምሽት እና ሌሊት የሚያሳልፉት ጊዜ የተመቻቸ እንዳልሆነ ያመለክታል። በሌላ በኩል ከወር አበባ ጋር ወደቤታቸው ለመግባት ቢሞክሩ በልማዱ ይከሰታሉ የሚባሉ ችግሮችን አምነው በመቀበላቸው አደጋ እንዳይደርስ፣ ቤተሰባቸውንም ከመቅሰፍት ለመጠበቅ ሲሉ ይህንኑ አስቸጋሪ ሕይወት ይገፉታል።

በዚህ ወቅት ሴቷ የምትመገብበትም ሆነ የምትጠጣበት እቃ ለብቻ ነው። በባህሉ ትንንሽ ልጆች እናታቸው ዘንድ ሄደው መጫወት ይችላሉ። በተለይ ህፃናት እና ለአቅመአዳምና ሄዋን ያልደረሱ ልጆች አብረዋትም ሊመገቡ ይችላሉ ፤ ነገር ግን ወደቤት በሚመለሱበት ጊዜ ወደቤት ከመግባታቸው በፊት ግራዋና ሌሎች በአካባቢያቸው የሚያገኟቸው ቅጠሎች እጃቸውን መቀባት ወይም ታጥበው መግባት ይኖርባቸዋል። ይህም የመንጻታቸው ምልክት ነው። በአንጻሩ ባሏ፣ አባቷ ወይም ሌሎች ወንዶች እርሷ የነካችውን ኢቃ እንኳን ከነኩ እከክ በእከክ ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል፤ ዐይናቸው ይጠፋል፤ ከዚህም አልፎ ይሞታሉ የሚል እምነት አለ።

[14] ቃለመጠይቅ፣ወ/ሮአትሬደንብሾ፣ 29/3/2010 ዓ.ም።

የጻራ ብሄረሰብ ተወላጅ የሆነችው መረጃ አቀባይ[15] እንደነገረችን “ማኅበረሰቡ ብቻ ሳይሆን ሴቷም ብትሆን የወር አበባ ላይ እያለች እቤትዋ ውስጥ ብትቀመጥ፣ ምግብ አብስላ ቢበሉ ቤቱ ይረክሳል፣ ልጆቼ ይታመማሉ፣ ባለቤቴ አይኑ ይጠፋል፣ እንዲያውም ሊሞት ይችላል” የሚል ፍራቻ አላት፤ ይህም የእርሷ ብቻ ሳይሆን የሁሉም የወር አበባ የሚያዩ ሴቶች የጋራ ጉዳይ እንደሆነ ገልጻልናለች።

የወር አበባ መጥቶባቸው በጊዜያዊ ማረፊያ ውስጥ ተለይተው እንዲቆዩ የሚደረጉ ሴት ልጆች ወይም እናቶች በእጅ የሚነኩት ዕቃም ሆነ የሚመገቡት ምግብ እዚያ ማረፊያ ውስጥ ያለውን ብቻ ነው። ምግብም ሆነ መጠጥ ሊያቀብላቸው የሚፈልግ ቢኖር እንኳ የእንሰት ቅጠልን በመጠቀም ያቀብላቸዋል፤ ምክንያቱም ከመኖሪያ ቤት የመጣውን እቃ ሴቷ ከነካችው ይበከላል ተብሎ ስለሚታመን እና ተመልሶ እመጣበት ቤት እንዲመለስ ስለማይፈለግ ነው።

መረጃ አቀባዮች[16] እንደሚሉት ባሁኑ ጊዜ በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች አማካይነት በሚሰጥ ትምህርት ምክንያት ተስፋ ሰጪ ለውጦች እየታዩ ቢሆንም ከጉዳዩ ጋር የተያያዘው እምነት ስር የሰደደ በመሆኑ በተለይ በገጠራማ አካባቢዎች የጉዳዩ አስከፊነት ቀጥሏል። በሌላ በኩል በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የጉዳዩን አስከፊነት ለማሳየት ሙከራዎች ቢኖሩም በማኅበረሰቡ ዘንድ አዎንታዊ ምላሽ እንደሌለው የሚድያ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ። ለምሳሌ አንድ የሚዲያ ባለሙያ የሆነው መረጃ አቀባይ[17] በመረጃ አሰባሰብ ወቅት እንደገለፀው በአንድ ወቅት ከወር አበባ ጋር በተያያዘ በማኅበረሰቡ ዘንድ ስላለው ችግርና ማኅበረሰቡ የባህሪይ ለውጥ ማምጣት እንዳለበት የሚመክር ፕሮግራም አዘጋጅቶ እንደነበር፣ ነገር ግን በወቅቱ ባህላቸውን የሚጎዳ ነገር እንደተናገረ አድርገው እንደወሰዱት የሚያመለክቱ የተለያዩ አስተያየቶችን አስተናግዶ ነበር። ከአስተያየቶቹ በተለይ አንድ አባት “እከክ በእከክ እንድንሆን ትፈልጋለህ ወይ?” እንዳሉት ባለሙያው ነግሮናል።

በከተማ አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች በተለይ በካፋ አሁን አሁን እቤት ሆነው የወር አበባ ጊዜአቸውን የሚያሳልፉ እንዳሉ ከመስክ የተገኙት መረጃዎች ያመለክታሉ። ነገር ግን ከቤት ባይወጡም መኝታ እንደሚለዩ ይገልፃሉ። ይህንን አስመልክቶ ወ/ሮ መሰረት ሲገልጹ፡-

> የወር አበባ በምታይባቸው ቀናት ውሎዋም አዳርዋም ለወር አበባ በተዘጋጀው ቤት ውስጥ ነው፣ ከዚያ በፊት ወደቤት አትመጣም። በአሁን ጊዜ በተለይ በከተማ ፊት ለፊት ወይም ሳሎን ላይ ባትወጣም ለአባወራ የሚቀርበውን ነገር ባትነካውም እራስዋ በቤትዋ ነው የምትጨርሰው። ከተማ አካባቢ የሚኖሩ ሴቶችም ቢሆኑ ከቤት ባይወጡም መኝታ ይለያሉ። በገጠር የሚኖሩት ግን ባህል ነው ብለው ስለተቀበሉት ጉዳቱን እንኳን በግልጽ አውጥተው አይናገሩም[18]።

[15] ሙላ ሙልጊቲ (ቃለመጠይቅ፣ ታህሳስ 2012 ዓ.ም)

[16] ወርቁ ወ/ማሪያም ካፋ፣ ሲስተር አየለች ተረፈ፣ ናኦ ፣ ሲስተር አዛለች በየነ፣ ናኦ፣ ታከለ በየነ፣ ናኦ፣ ወይኒቱ (ቃለ መጠይቅ 2014 ዓ.ም)

[17] ታከለ በየነ፣ ቃለመጠይቅ (2014)

[18] መሰረት መኩሪያ፣ (ቃለመጠይቅ፣2014)

ምንም እንኳን ጊዜው ቢሻሻልና የአስተሳሰብ ለውጦች አሉ ቢባልም ከወር አበባ ጋር የተያያዘው ልማድ ግን የቀጠለ መሆኑን ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል። ወንዶችም ቢሆኑ ትክክለኛ ነው ብለው በማመናቸው ማንም ሳይነግራቸው ባህሉን እንደሚጠብቁ እርግጠኛ ሆነው ይናገራሉ[19]።

### 4.4. ከወር አበባ ጋር የተያያዘ የመንጻት ስርዓት

በነዚህ ማህበረሰቦች ዘንድ አንዲት ሴት ሳታውቅ ድንገት በቤትዋ፣ በሰው ቤት ወይም ባለውቃቢ ቤት እያለች የወር አበባ ከመጣባት ቤቱ መንጻት አለበት ተብሎ ይታመናል። በአጋጣሚ ወይም በመፍራት የወር አበባ መጥቶባት እቤት ውስጥ ብትሆንና ሳትወጣ ብትቆይ ቤት ውስጥ ችግር መኖሩንና መንጻት የሚያስፈልግ እንደሆነ አመላካች የሆኑ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ ተብሎ ይታመናል። የወር አበባ የመጣባት ሴት ምናልባት ንክኪ ካለ ቃልቻ ቤትም ከገባች ቤት ውስጥ ጉንዳን የሚመጣበት፣ እባብም የሚታይበት አጋጣሚ እንዳለ መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ። ይህንን አስመልክቶ የናኦ መረጃ አቀባያችን[20] ሲገልጹ፡-

> አንድ ጓደኛዬ የባለቃልቻ ልጅ ነው። ለበዓላት አንዳንድ ነገሮች ሲደረጉ ከትምህርት ቤት ስንመለስ እንሄዳለን። በቃልቻው ቤት ግቢ አንደኛ አጥር አለ፤ ሁለተኛ አጥር አለ። አንዲት ጎረቤት በክብር ተጠርታ ነው የመጣችው። በክብር ተጠርታ መጥታ በወር አበባ የለበሰችውን ልብስ ነው ለብሳ የመጣችው። መጥታ ሁለተኛ አጥር አከባቢ ነበር የተቀመጠችው። አባብ ከቃልቻው ቤት ቀጥ ብሎ ይመጣል፤ ጥቁር እባብ ነው። መጥቶ ሴትየዋ ጀርባ ላይ ደርሶ ሊነድፋት ሲል ሴትየዋ ደንግጣ ሮጣ ወጣች፤ ተከትሏት ወጣ፤ ሲጠይቋትም በወር አበባ ጊዜ ተጠቅማው የነበረውን ልብስ ሳታውቅ ለብሳ መምጣቷን ተናገረች። ወይኔ እያለች ስትጮህ አይቻለሁ፤ ጥፋቷ በጩኸት ይወጣል ስለሚባል።"

በማለት የተማሪነት ህይወት ገጠመኛቸውን ነግረውናል። በማህበረሰቡ ከወር አበባ ጋር በተያያዘ ችግሮች ቢከሰቱ መንጻት አስፈላጊና ግዴታም እንደሆነም ይናገራሉ። በመሆኑም እንደየማህበረሰቡ የመንጻት ስርዓቱ ይፈጸማል።

የመንጻት ስርዓቱ በተለይ በናኦ ብሔረሰብ ዘንድ የሚካሄደው በደም ነው። "በደም ታጠበ (ነጻ)" የሚባለው ደግሞ መረጃ አቀባዮች እንደሚሉት እንደየደረጃው በበሬ (በተለይ በባለቃልቻ ቤትና አካባቢው የወር አበባ ፍሰት ሲያጋጥም)፣ በፍየል ወይም በዶሮ (በግል መኖሪያ ቤትዋ ወይም በሌሎች ቤት የወር አበባ ከመጣ) ሊሆን ይችላል። የማንጻት ሥርዓቱን የሚያካሂዱትም የተመረጡ ሰዎች ናቸው። መረጃ አቀባዮች[21] እንደሚሉት የመንጻት ስርዓቱን የሚያካሂደው ከነሱ ጎሳ ውጪ የሆነ ሰው ነው። እኚሁ መረጃ አቀባይ እንዳሉት "በናኦዎች ዘንድ የወር አበባ የመጣባት ሴት ለማንጻት የሚመረጠው ሰው ሚዜ፣ የሴቷ የእህት ልጅ ወይም ቤት የሚያጸዱ አሉ፤ ሺኬስ የሚባሉ ከናኦ ጎሳዎች ውስጥ አንዱ ነው። በነሱ አማካኝነት የመንጻት ስርዓቱ የሚፈጸም ሲሆን ለነሱ የሚደረግ ነገር አለ፤ ዶሮ ሊሆን ይችላል፣ ፍየል ሊሆን ይችላል ወይም ደረቅ ብር ሊሆን ይችላል፤

[19] ታምራት ባዩ፣ ቃለ መጠይቅ 2014 ዓ.ም

[20] ታከለ በየነ፣ ታህሳስ 9፣2014 ዓ.ም

[21] ወይኒቱ ወልዴ፣ ካሰች ተካ (ቃለመጠይቅ፣ 2011 ዓ.ም)

በማቅረብ የመንጻት ስርዓቱ ይካሄዳል።"[22] በባህሉ መሰረት የሚያነፃው ሰው ለመንጻት ስርዓቱ የቀረበውን ፍየል ጆሮ ይቆርጥና ደሙን ሴቷ ተገኝታ በነበረበት ቤት እንዲፈስ (እንዲንጠባጠብ) አድርጎ ፍየሉን ወስዶ ይሔዳል። ለመንጻት ስርዓቱ የቀረበው መስዋዕት የሴትዋን ሃጥያት ይዞ ይሄዳል[23]፤ ቤቱም ይነጻል ቤተሰቦችዋም ከመርገምት የጸዱ ይሆናሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው። የቤቱ ባለቤቶች ፍየሉንም ይሁን ዶሮውን ወይንም በሬውን አይፈልጉትም፤ አይመገቡትም። የሚያነጻው ሰው እንደየሴትዋ ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማንጻት የተሰጠውን ዶሮ ወይም ፍየል ይይዛል፤ በተጨማሪም በተለይ በካፋ ብሔረሰብ የሚያነጻው ሰው ከፍየሉ ጋር ከግራዋ (ቅጠል)፣ ኡፎ፣ ሊጦ (የሳር አይነቶች) ውህድ በማዘጋጀት አካባቢውን ይረጫል። ከዚያም በገባበት በር ሳይሆን በሌላ በር ይወጣል፤ በዚህ ጊዜ ቤቱ ነጽቷል ተብሎ ይታመናል። የቤቱ ሙሉ በሙሉ መጽዳት የሚረጋገጠው ለመንጻት የቀረበው እንስሳም ሆኑ የሚያነጻው ግለሰብ መጀመሪያ ከገባበት አቅጣጫ በተቃራኒው ሲያልፍ ነው።

በባህሉ መሰረት ለሴቷ በግል ከተሰራው ቤት ውጪ የወር አበባ ፍሰት መከሰት በዋናነት በቃልቻ ቤት የዚህ አይነቱ ሁኔታ መፈጠር ጥፋት ተደርጎ ስለሚታመን ያጠፋችው ሴት የሚወሰንባትን ውሳኔ ተቀብላ መፈፀም አለባት። ካልሆነ ግን ውቃቢው ጉዳት ያደርስባታል፤ አይኗ ይታወራል ተብሎ ይታመናል። ለባለውቃቢውም ጥሩ አይሆንም ስለሚባል የመንጻት ስርዓቱ መከናወን ይኖርበታል።

በሌላ በኩል ሴቷ ድንገት ሳታውቀው መኖሪያ ቤቷ ውስጥ የወር አበባ ከመጣባት ጮሀ ትወጣና ትናገራለች፤ ከዚያ በቤቱ የመንጻት ስርዓት ይከወናል። በጻራ ማኅበረሰብ ዘንድም እንዲሁ በወር አበባ ላይ እያለች የማይፈቀድ ቦታ በመግባቷ፣ ቃልቻ ቤት ወይም የወር አበባ እንደመጣባት እያወቀች ለባሏ ምግብ ሰርታ ካበላች የምትቀጣው ሽማግሌዎች ተቀምጠው ሲሆን እንደ መረጃ አቀባዮች ገለጻ የወር አበባ የታያት ሴት አንድ ቀፎ ከነንቡ ገዝታ በማቅረብ የመንጻት ስርዓት እንዲካሄድ ይወሰናል። ባሏ ወይም ተበዳዩ ባለቃልቻ ይቀመጣል፤ ሴቷም በንብ ቀፎው ፊት ለፊት እንድትቀመጥ ይደረጋል። ለማንጻት ስርዓቱ ከዋኔ የተመረጠው ሰውም በቀረበው የንብ ቀፎ ፊት ለፊት ጦር ይዞ ንቡን ለመበተን ይቆማል።

ይህ የንብ ቀፎ በጦር[24] ተከፍቶ የሚበተነው በባህሉ በተወሰኑ ሰዎች ነው። እነዚህም ሰዎች (የንብ ቀፎውን ካለበት የሚያመጣ እና የሚከፍተው) ወጣት የሆነ የሴቷ የስጋ ዝምድና[25] ያለው ስርአቱን የሚያስፈጽመውና ስልጣን የተሰጠው ደግሞ ከጻራ ጎሳዎች መካከል ቢርሰሳ የተባለው ሲሆን እሱም ለዚሁ ብሎ የተሰጠውን ጦር ይዞ በስርዓቱ ላይ ይገኛል። የንብ ቀፎውን ከመክፈቱ በፊት ጦሩን

---

22 ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ 9፣2014 ዓ.ም

23 ለመንጻት ስርዓቱ የሚሰጠውን ዶሮ ወይም ፍየል የሚያነጻው ሰው ይዞ ይሄዳል፤ ቢፈልግ ቢሸጠው አርዶም ቢበላው ምንም የሚያደርስበት ችግር የለም ተብሎ ይታመናል፡፡

24 በጻራዎች ዘንድ ጦር ከባህላዊ እምነት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው የክብር መገለጫ ነው፡፡ በባህሉ በተለያዩ አውዶች የተለያዩ የጦር አይነቶች አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡፡ በማንጻት ስርዓቱ ላይ የሚገኘው የተጠቀሰው ጎሳ አባል ይዞት በስርዓቱ ላይ የሚገኘው ጦር በውርስ የሚገኝ ነው፡፡

25 በባህሉ በተለያዩ እምነታዊና ባህላዊ አጋጣሚዎች የስጋ ዘመድ ይመረጣል፡፡ ለሚዜ የሚመረጠው የስጋ ዘመድ ነው፤ በመንጻት ስርዓቱ ላይም ንቦች ከቀፎ እንዲወጡ በማድረግ ድጋፍ የሚሰጠው የስጋ ዘመድ ነው፡፡ በተለይ በዚህ አውድ በሴቷ ላይ የከፋ አደጋ ቢደርስ ለምሳሌ በንብ በመነደፍ ምክንያት ከፍተኛ አደጋ ቢከሰት ሃላፊነቱን ቤተሰብና ቤተዘመድ እንዲወስድ በሚል ነው፡፡

ይዞ በዙሪያው ያሉ አካባቢዎች ስም እየጠራ "ከእኛ ይራቅ" በማለት ወደተጠቀሱት ቦታዎች ይሂድ እያለ "እኛ አካባቢ ይሄ ሁለተኛ አይሰማ" ይላል። በዚህ ጊዜ ንቦቹ እንዲወጡ የማሩን ቀፎ በጦሩ ይነካዋል። ንቦቹም ወጥተው የተቀመጠችው ሴት ላይ እያረፉ እየበረሩ ይሄዳሉ፤ የሚነድፏትም ከሆነ ትነደፋለች። በባህሉ መሰረት ለመከላከል ብትሞክር ከሃጥያቷ አልነጻችም[26] ስለሚባልም የሚደርስባትን በንቦች የመነደፍ አካላዊ ጉዳት አምና ትቀበላለች።

## 5. ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት ተፈጥሮአዊ ክስተት የሆነው የወር አበባ ከማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር ባለው ጥብቅ ቁርኝት የተነሳ በተጠኚው ማኅበረሰብ ዘንድ ያለውን ቦታና የዚህ ክስተት ባለቤት የሆኑ ሴቶችም በማኅበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ቦታ ለማየት ተችሏል። በካፋ ማኅበረሰብ ዘንድ ከወር አበባ ጋር ተያይዞ ሲከወንና ሲተገበር የመጣው ባህላዊ ድርጊት እና እምነት አሁንም እየተተገበረ ይገኛል። ከመስክ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱትም በካፋ በገጠር አካባቢ በብዛት፣ በጻራ እና በናኦ ማኅበረሰብ መኖሪያ አካባቢዎች በገጠር አካባቢ የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች አሁንም ይህን ልማዳዊ ድርጊት ሲተገብሩት ይስተዋላል። በትንተናው መሰረት የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል።

አንዲት የወር አበባ የመጣባት ሴት ከመጣበት ቀን ጀምሮ ከቤት ወጥታ ለዚሁ በተዘጋጀላት መቆያ ትቆያለች። በነዚህ ቀናት ከቤቷ ምግብ ወስዳ መመገብ አትችልም። እርሷ የምታዘጋጀውን ሌላ ሰው አይበላም፤ አይጠጣም። የሰው ቤትም መግባት አትችልም።

የወር አበባንና የወር አበባ የመጣባትን ሴት የርኩሰት ወይም ያለመንጻት ምልክት አድርጎ የመመልከት እምነት መኖሩን ከመስክ የተገኙት መረጃዎች አመላክተዋል። በነዚህ ማህበረሰቦች እምነት አንዲት ሴት የወር አበባ ላይ እያለች እቤት ብትገባና እርሷ ያዘጋጀችውን ባለቤቷ ቢመገብ እከክ ይለቅበታል፤ አይኑም ይታወራል ተብሎ ይታመናል፤ ይህም ሴቶች የወር አበባ በሚያዩበትና በማያዩበት ጊዜ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ቦታ እና ውክልናቸው የተለያየ መሆኑን ያመለክታል።

አንዲት ሴት የወር አበባ በምታይባቸው ቀናት የምታርፍበት መኝታ ምቾት አይኖረውም፤ ምግብም በበቂ ሁኔታ አታገኝም፤ ለብቻ እንድትሆን መደረጉ ደግሞ የመለየት እና የመገለል ስሜት እንዲሰማት ምክንያት እንደሆነ መረጃዎች አመላክተዋል።

ሴቷ ሳታስበው ድንገት የወር አበባ ቢመጣባት የደም ፍሰቱ በተከሰተበት ስፍራ ወይም ቦታ የመንጻት ስርዓት መካሄድ እንደሚኖርበት በትንተናው ክፍል ተገልጾአል። ለመንጻቱም በሴቷ በኩል የሚቀርቡት ዶሮ፣ ፍየል፣ ከብት ወይም ገንዘብ እንደሆኑ ትንተናው አመላክቷል።

በነዚህ ብሔረሰቦች ዘንድ ሴት ልጅ የወር አበባ በምታይባቸው ቀናት ከድርጊቶች እና ከቁሶች ንክኪ እንድትታቀብ ትደረጋለች። ለምሳሌ የቤትን ምሰሶ ማየት በአካባቢውም ማለፍ የወንዱን ክብር እንደመዳፈር ተደርጎ ይታመናል። በማኅበረሰቡ ዘንድ የወር አበባን በሚመለከት የጋራ እሳቤ ቢኖርም በጉዳዩ ላይ በግልጽ የመወያየት ልምዱ የለም፤ ከዚያ ይልቅ የሴቷ የግል ጉዳይና በጉዳዩም ተጠያቂ የማድረግ እምነት እንዳለ ትንተናው አመላክቷል።

---

[26] ጻራዎች ንብ ጣፋጭ ማርን የምትሰጥ በመሆንዋ ለንብ ልዩ ቦታ አላቸው፡፡ በመሆኑም በንብ መነደፍ ከጥፋት መጽዳት ወይም የመንጻት ተምሳሌት ነው፡፡

የወር አበባ ከተፈጥሮአዊነቱ ይልቅ ባህላዊነቱ ጎልቶ የሚታይ በመሆኑ ሴቶች በወቅቱ የተለየ ተደርገው ይታያሉ። ይህም ሆኖ በባህሉ የተጫነባቸው ችግር እንዳለ ቢሆንም በአቅራቢያቸው የሚገኙ ሌሎች ሴቶች እርስ በርስ ለመረዳዳት የሚያደርጉት ጥረት መልካም የሚባል እንደሆነ መረጃዎች አመላክተዋል።

ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው የወር አበባ እና ክልከላዎቹ በዋናነት በሴቷ በመቀጠል ደግሞ ሴቷ በወጣችበት ቤተሰብ እንዲሁም ማኅበረሰብ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያደርሱት ተጽእኖ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ጉዳዩ የሚመለከታቸው በአጠቃላይ በማህበረሰብ፣ በሴቶች እና ቤተሰብ ላይ የሚሰሩ አካላት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ቢሰሩ መልካም ነው የሚል አስተያየት አለን። በተጨማሪም የወር አበባ ጉዳይ የሰው ጉዳይ ነውና ሰውን ጉዳያቸው ባደረጉ የጥናት መስኮች ውስጥ ባሉ አጥኚዎች ከስርዐተ ጾታ፣ ከስነልቦና እና ከሌሎች የጥናት መስኮች አኳያ ጉዳዩ ቢጠና ሴቶችን ከእንዲህ አይነቱ ተጽእኖ ለመታደግ፣ በማህበረሰቡ ዘንድም ለውጥ ለማምጣት አንዳች ፋይዳ ይኖረዋል።

## ማጣቀሻ ጽሑፎች


የካፋ ዞን ባህልና ቱሪዝም የጽሑፍ መረጃ፣ ታህሳስ 8፣ 2014 ዓ.ም

Abdul-Majeed, R. K. (2016). Taboo Words Vs. Social Deixis: A sociolinguistic Analysis of *La Justiceor The Cock that Crew*: A Play from the Theatre of Ridiculous. University of Baghdad: *J. Of College Of Education For Women*

Allan, K. and Burridge, K. (2006). *Forbidden Words: Taboo and the Censoring of Language*. Cambridge: Cambridge University Press.

Aragon, A. P. (2004). Femininity. In S. Loue & M. Sajatovic (Eds.), *Encyclopedia of Wwomen's Health*. (pp. 484-486). New York: Kluwer Academic/Plenum.

Balew Z. (2016).“Menstrual hygiene management and associated factorsam ong highschool girls: a case of Bahir Dar city administration”. College of Health Sciences: School of Allied Health Sciences, Department of Nursing And Midwifery

Bhartiya, A. (2013). “Menstruation, Religion and Society. *International Journal of Social Science and Humanity*, Vol. 3, No. 6.

Brantelid, Ida E., Nilver, H. and Alehagen S. (2014). Menstruation During a Lifespan: A Qualitative Study of Women’s Experiences**.** *Health Care for Women International,* (35),6, 600-616.

Botello-Hermosa, A. and Casado- Mejia, R. (2015.). Ears And Concerns Related to Menstruation: A Qualitative Study From The Perspective Of Gender. *Text Context Nursing, Florianópolis*.

Burnet Institute, International Women’s Development Agency and Water Aid. (2017).The Last Taboo Research on menstrual hygiene management in the Pacific: Solomon Islands, Fiji, and Papua New Guinea Final report.

Dammery, S. (2016). *First Blood: A Cultural Study of Menarche*. Monash University Publishing.

Danielsson, A. (2017). The Role of Menstruation – a Case Study amongst Women from Nakwa Village in Tanzania. Södertörn University,

School of Natural Sciences, Technology and Environmental Studies, Development and International Cooperation, Bachelor Thesis.

Dejene N. D. (2009. Gender and Culture in Southern Ethiopia: An Ethnographic Analysis of Guji-Oromo Women's Customary Rights. *African Study Monographs*, 30(1): 15-36.

Duveen, G., & Lloyd, B. (1990). *Social Representations and the Development of Knowledge*. Cambridge: Cambridge University Press.

Dong, M., Jurgens, D., Banea, C. and Mihalcea, R. (ND) Perceptions of Social Roles Aacross Cultures. USA, University of Michigan.

Dorson, R. M. (1972). *Folklore and Folk life: An Introduction*. U.S.A: the University of Chicago Press.

Finnegan, Ruth. (2012). *Oral Literature In Africa* Open Book Publishers.

Gennep, A. van (1960) [1909] *The Rites of Passage*, Chicago: Chicago University Press.

Gómez-Sánchez, PI, Pardo- Mora, YY, Hernández-Aguirre, HP, Jiménez-Robayo, SP and Pardo-Lugo, JC. (2012). Menstruation in History. *Invest Educ Enferm.*

Kothari, C.R. (2004). *Research Methodology: Methods and Techniques*. New Age International P) Limited, Publishers.

Mehta, Clare M. & Henry, Victoria. (2020). Feminity. https://www.researchgate.net/publication/314160166.

Mengistu B. (2018) "Assessment of age at menarche and menstrual cycle pattern among adolescent school girls in Gamo Gofa Zone, Southwest Ethiopia". MA Thesis.

Mojumder, M. (2020). The Role Of Women In The Development of Society. *Journal of Critical Reviews*. Vol 7, Issue 02.

Mohamed, Y., Durrant, K., Huggett, Ch., Davis, J., Macintyre, A., Menu, S., Wilson, J. N., Ramosaea, M., Barrington, Dani J., McSkimming, D., Natoli, Lisa, and Sami, Michael. (2018). A qualitative exploration of

menstruationrelated restrictive practices in Fiji, Solomon Islands and Papua New Guinea.*Plos One.* https://doi.org/10.1371/journal.pone.0208224

Mondragon N. I. and Maitane, B. T. (2019. Understanding menstruation: Influence of gender and Ideological Factors: A study of young people's social representations. University of the Basque Country *UPV/EHU,* Spain.

Moscovici, S. (1963). "Attitudes and opinions". *Annual Review of Psychology, 14*, 231–260.

Muriricho, A. (ND). "Menstrual Lives in Rural Ethiopia: Experiences of rural Ethiopian girls and women with managing menstruation throughout the different phases of their menstrual lives in Basona Werana, Amhara, Ethiopia". Recommendations for COWASH based on Master Thesis.

Nahia, I. Mondragon and Maitane, Txertudi, B. (2019). Understanding Menstruation: Influence of Gneder and Ideological Factors: A Study of Young People's Social Representations. *Feminism & Psychology.* Sage Publication.

Obi, C. (2005). *Environmental Movements in Sub-Saharan Africa: A Political Ecology of Power and Conflict*. UN Research Institute for Social Development, Civil Society and Social Movements Programme, Paper No. 1.

Okopehu (1992). *African Oral Literature፡ Backgrounds, Character and contunity.* USA: Bloomington and Indianapolis: Indiana University press.

Sims, Martha and Stephens, Martine. (2005). *Living Folklore; An Introduction to The Study of People and Their Traditions*. Lagan Utah state University Press.

Steiner, Franz .1956. *Taboo.* London: Cohen and West (repr. Hannondsworth: Penguin.

UNICEF. (2013). *Menstrual Hygiene in Schools in 2 countries of Francophone West Africa Burkina Faso and Niger Case Studies*.

Upashe, S. P. Tesfalidet T. and Jalane M. (2015). Assessment of knowledge and Practice of Menstrual Mygiene among High School Girls in Western Ethiopia. *BMC Womens Health* 15:84.

Wagner, W., Gerard, D., Robert, F., Sandra, J., Fabio, Lorenzi-C., Ivana, M., Diana R. (1999). Theory and method of social representations. *Asian Journal of Social Psychology.v.* 2: pp.95–125.

Wall, L. Lewis, Kibrom T., Alem D. and Shewaye B. (2018) . "Tending the 'monthly flower:' a qualitative study of menstrual beliefs in Tigray, Ethiopia". *BMC Women's Health* https://doi.org/10.1186/s12905-018-0676-z

Walton, S. (2013). Does Menstruation Hinder Women's Empowerment? Working Toward Social Change In South India. *Syracuse University Honors Program Capstone Projects. 50*. https://surface.syr.edu /honors_capstone/50.

Webster, Hutton. (1942). *Taboo: A Sociological Study*. London: Oxford University Press.